# Mutual Assistance Association for the Ethiopian Community Inc., In DFW

## የኢትዮጵያውያን የጋራ መረዳጃ ማህበር

9858 Plano Rd, Suite#110 Dallas, TX. 75238. www.maaecdallas.org 214-321-9992

### በኢትዮጵያውያን የጋራ መረዳጃ ማህበር ስራ አስፈጻሚ ኮሚቴ በዳላስ ፎርት ዎርዝ
### የወቅቱን የአገራችንን ሁኔታ አስመልክቶ የተሰጠ የአቋም መግለጫ

ዳላስ ቴክሳ ሴፕቴምበር 3፣ 2016

ኢትዮጵያ በረጅም ዘመን ታሪኳ በክፉም ሆነ በበጎ አብሮ የመኖር የበለጸገ ባህል ያካበተች አገር ስትሆን ሕዝቡም በታሪኩ የገጠሙትን ዘርፈ ብዙ የሆኑ ችግሮችን በአንድነት ተቀናጅቶ በድል አድራጊነት የተወጣ ኩሩና ታላቅ ሕዝብ ነው። በዘርና በሃይማኖት ሳይከፋፈል ለዘመናት አብሮ የመኖር ባህሉን ያስመሰከረና በምሳሌነትም የሚጠቀስ እንዲሁም በመንግስት ምስረታ ታሪክ ቀደምትነት ካላቸው ጥቂት አገሮች ዝርዝር ውስጥ የሚካተት ታላቅ ሕዝብ ነው።

የአገሪቱንም ሉአላዊነት በማስጠበቅና ክብሩንም ባላማስደፈር በርካታ ታሪክ ያስመዘገበ ኩሩ ሕዝብ ነው። የተለያየ አቋም የነበራቸው መንግስታት የተፈራረቁበት ጠንካራ ሕዝብ ሲሆን መጠኑ ይለያይ እንጂ ሁሉም መንግስታት አስተዳደራዊ በደል አድርሰውበታል። በአሁኑ ወቅት ያለው መንግስት ባህርይ ግን የኢትዮጵያ ህዝቡ በታሪኩ ከሚያውቃቸው መንግስታት ፍጹም የተለየ ለመሆኑ ታሪካዊ ማስረጃዎች ያሉ ሲሆን፤ በዘርና በቋንቋ ላይ የተመሰረተ መንስግስት ማዋቀሩን ፤ የአንድን ዘር የበላይነት በተግባር ማረጋገጡን ፤ ከህዝብ የሚነሱትን ማንኛውም ጥያቄዎችን በሃይል መጨፍለቅ እንደዓነተኛ መፍትሄ መውሰዱን በተከታታይ አረጋግጧል።

በዚህ ጭካኔ የተሞላበት የመንግስት ተግባር የትኛውም የህብረተሰብ ክፍል ማለትም በለጋ እድሜ ያሉ ህጻናት ፤ ሴቶች እና አረጋውያን ግንባር ቀደም ተጠቂዎች ሆነዋል እየሆኑም ነው። ይህ እስካሁን ያየነው ግፍና በደል አልበቃ ብሎ በቅርቡ መንግስት ለመከላከያ ሰራዊቱ የሰጠው ተደጋጋሚ የሃይል መውሰድ እርምጃ ትዕዛዝ በታሪክ ይቅር የማይባልና ሃላፊነት የጎደለው አሳፋሪ ድርጊት መሆኑን ሕዝቡ ብቻ ሳይሆን የሰብአዊ መብት ጉዳይ የሚመለከታቸው አለም አቀፍ ድርጅቶችም ሳይቀሩ በአጽንኦት አውግዘውታል ኮንነውታልም።

በዳላስና ፎርት ዎርዝ አካባቢ የምንገኝ የኢትዮጵያውያን የጋራ መረዳጃ ማህበር የስራ አስፈጻሚ ኮሚቴ 15 ኛውን የኢትዮጵያ ቀን ለማክበር በዝግጅት ባለበት በአሁኑ ወቅት በአገራችን ውስጥ እየተካሄደ ያለውን አሰቃቂና አደገኛ ሁኔታ ላይ ተወያይቶ የሚከተለውን የአቋም መግልጫ አውጥቷል።

1. መንግስት ለሰራዊቱ የሰጠውን የንጹሃንን ደም የማፍሰስ ትዕዛዝ በአሰቸኳይ እንዲያቆምና ሰራዊቱም ወደ ጦር ሰፈሩ እንዲመለስ እንጠይቃለን።
2. የመከላከያ ሰራዊቱም ሕገመንግስቱ የሰጠውን አገር የመጠበቅ ድርሻ ከማስፈጸም ውጪ በገዛ ወገኑ ላይ ያዞረውን አፈሙዝ እንዲመልስ እንዲሁም ከወገኑ ጋር እድዲቆምና ወገኑንም እንዲጠብቅ ጥሪ እናቀርባለን።
3. መንግስት በአሁኑ ወቅት ያለውን ችግር በሃይል ከመፍታት እርምጃው ተቆጥቦና የሕዝብን ጥያቄ በአግብቡ ተቀብሎ ሕዝባዊ መሰረት ያለው መፍትሄ እንዲሰጥ እናሳስባለን።
4. በተለያዩ ጊዜያት መብታቸውን በመጠቀም ሃሳባቸውን ለመግለጽ በወጡ ሰላማዊ ዜጎች ላይ በተወሰደው እርምጃ ክቡር ሕይወታቸውን ላጡ፤ አካላቸው ለጎደለና ንብረታቸው ለወደመባቸው ተመጣጣኝ የሆነ ካሳ እንዲከፈላቸው እንጠይቃለን።
5. መንግስት ሕገመንስግቱ ለሕዝቡ የሚፈቅድለትን የተለያዩ መብቶች እንዲያከብር እንዲሁም የፖለቲካ እስረኞችን ፤ ጋዜጠኞችንና፤ የህሊና እስረኞችን በአስቸኳይ እንዲፈታ እንጠይቃለን።
6. በአሁኑ ሰአት መንግስት እይፈጸመ ያለውን ህዝብን ከህዝብ ጋር የማጋጨት እኩይ ተግባር እንዲያቆም እንጠይቃለን።
7. በየትኛውም ዘርፍ የሚገኙ የሃይማኖት አባቶች በሕዝብ ላይ የሚደርሰውን ግፍና በደል በአስቸኳይ እንዲቆም የመፍቴሄው አካል እንዲሆኑ ጥሪያችንን በአክብሮት እናቀርባለን።

ኢትዮጵያ ለዘላለም ትኑር!

በኢትዮጵያውያን የጋራ መረዳጃ ማህበር በዳላስ ፎርት ዎርዝ ስራ አስፈጻሚ ኮሚቴ